*<u>ይህችን የመልስ ምት ያንብቡ</u>*

## *<u>ቀን ቀን ድስት ጠግኖ ማታ ማታ ድልድይ ማፍረስ ?</u>*

*የቀድሞው የኢሃዴግ ማስታወቂያ ሚ/ር በረከት ስምዖን ለምርጫ 1997 ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ሙግት በገጠሙበት አንድ ፕሮግራም ላይ ሲናገሩ፡ “ ኢሃዴግ የዲሞክራሲን ጎዳና በመቀየስና በማራመድ የመጀመሪያ ድርጅት (መንግስት) እንደ መሆኑ ባለፉት አስራ 4 አመታት ምንም ስህተት አልሰራንም አንልም ነገር ግን ከስራነው ስህተት ይልቅ ጎልቶ የሚታየው የሰራነው በጎ ነገርና ልማት ነው፡፤ ይህ ሃቅ ግን ለተቃዋሚዎቻችን በፍጹም ሊታያቸው ያለመቻሉ በጣም ይሳዝናል፡፤ይሁን እንጂ የሕዝብ ድጋፍ ስላለን እንደ ጅማሪነታችን ጥፋትም ቢኖር ታርመን ጎልቶ በሚታየው ጥንካሬያችን ደግሞ እንገፋበታለን!!! “ ሲሉ በመዘባነን ይናገራሉ፡፤*

*ከተቃዋሚ ድርጅቶች ተከራካሪ አንዱ ለዚሁ ለማስታወኪያ ሚንስትሩ አነጋገር ምላሽ ሲሰጡ፡፤ እንዲህ ይላሉ።*
*“ ክቡር ሚ/ሩ እንዳሉት በትክክልም ለኛም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታየው ኢሃዴግ ካለማው ይልቅ ያጠፋው እጅግ የገዘፈ ከገነባው ይልቅ ያፈረሰው እጅግ የበዛ መሆኑ ነው። በዛም ላይ ማለቂያ የሌለው ውሸታቸው ሕዝብን አስመርሯል።*

*እስኪ ተመልከቱት ማታማታ ድልድይ ሲያፈርሱ አድረው ቀንቀን ድስት ጠጋኝ እያሉ በመዞር አሮጌ ድስት መጠገናቸውን ከልማት ቆጥረውት ይሆን ካጠፉነው ያለማነው ይበልጣልና .....የሚሉት? ለመሆኑ የአንድ ቤተሰብ ከርስ የሚሞላ ሰባራ ድስት መጠገን ነው ወይስ ሃገር የሚያገናኝ ድልድይ ማፍረስ ግዙፉ ተግባር? ድንቂም የልማት አውታር”..... በማለት መራራውን እውነት በተመልካች ሳቅ አጉመጥምጠው ካዋጧቸው በኋላ አስተያየታቸውን ሲያጠቃልሉ! “ ጅብ የማያውቁት ሃገር ሂዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ ነበር ተረቱ ዛሬ ማንንፈርቶ ኢያ ጅቦ በሚያውቁትም አገር ቁርበት አጥፉ ይል ጀመራ፡፤” ብለዋል።*